# የምግብ አያያዝ ባለሙያዎች ሪፖርት ማድረጊያ ስምምነት

የዚህ ስምምነት አላማ የምግብ አያያዝ ባለሙያዎች ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ሲከሰት ጉዳዩ የሚመለከተውን ኃላፊ (PIC) የማሳወቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው ማሳወቅ ነው፣ ስለሆነም PIC በምግብ የሚተላለፉ በሽታዎችን እንዳይተላለፍ ለመከላከል ተገቢ እርምጃዎችን መውሰድ ይችላል።

**ለPIC ሪፖርት ለማድረግ እስማማለሁ፦**

በስራ ቦታም ሆነ ከስራ ውጭ ማናቸውም የሚከተሉት ምልክቶች መታየት፣ መታየት የጀመሩበትን ቀን ጨምሮ፦

1. ተቅማጥ
2. ማስመለስ
3. የቢጫ በሽታ
4. ትኩሳት ያለው የጉሮሮ ህመም
5. በእጅ፣ አንጓ፣ የተጋለጠ የሰውነት ክፍል ወይም ሌላ የሰውነት ክፍል ላይ በኤንፌክሽን የተበከሉ የተቆረጡ ቦታዎች፣ ቁስሎች ወይም መግል የያዙ ጉዳቶች መኖር እና የተቆረጡ ቦታዎች፣ ቁስሎች ወይም ጉዳቶች በትክክል አልመሸፈን (ምንም ያክል ትንሽ ቢሆኑም እንደ እባጮች እና በኤንፌክሽን የተበከሉ ቁስሎች ያሉ)

የወደፊት የህክምና ምርመራ፦ በኖሮ ቫይረስ፣ ታይፎይድ (*Salmonella* Typhi)፣ ሺጌሎሲስ (*Shigella* spp. ኢንፌክሽን)፣ *Escherichia coli* O157:H7 ወይም ሌላ STEC ኢንፌክሽን፣ የታይፎይድ ያልሆነ *Salmonella* ወይም ሄፓታይተስ A (ሄፓይታተስ A የቫይረስ ኢንፌክሽን) በሚያዙበት ጊዜ።

የምግብ ወለድ በሽታ አምጪ ተህዋሲያን የወደፊት ተጋላጭነት፦

1. ለኖሮ ቫይረስ፣ ታይፎይድ፣ ሺጌሎሲስ፣ *E. coli* O157:H7 ወይም ሌላ STEC ኢንፌክሽን ወይም ሄፓታይተስ A መጋለጥ ወይም ማንኛውንም የተረጋገጠ የበሽታ ወረርሽኝ የመፍጠር ጥርጣሬ
2. ኖሮ ቫይረስ፣ ታይፎይድ፣ ሺጌሎሲስ የተገኘበት፣ በSTEC ኢንፌክሽን ወይም ሄፓታይተስ A ምክንያት የታመመ የቤተሰብ አባል።
3. የተረጋገጠ የኖሮ ቫይረስ፣ ታይፎይድ፣ ሺጌሎሲስ፣ *E. coli* O157:H7 ወይም ሌላ STEC ኢንፌክሽን ወይም ሄፓታይተስ A ወረርሺኝ ባለበት አከባቢ የተገኘ ወይም የሚሠራ የቤተሰብ አባል።

በSNHD 2023 የምግብ ደንቦች ስር እና በዚህ ስምምነት የሚከተለውን ለማክበር ያሉብኝን ሀላፊነቶች በተመለከተ አንብቤያለሁ (ወይም ተብራርቶልኛል) እና ተረድቻለሁ፦

1. ምልክቶችን፣ ምርመራዎችን እና ተጋላጭነትን የሚያካትቱ ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ሪፖርት ማድረግ፤
2. በእኔ ላይ የተጣሉ የሥራ ገደቦች ወይም ማግለያዎች፤ እና
3. ጥሩ የንጽህና ልማዶች።

የዚህ ስምምነት ውሎችን አለማክበር በምግብ ስራ ቦታው ወይም በምግብ ቁጥጥር ባለስልጣን ስራዬን አደጋ ላይ የሚጥል እና በእኔ ላይ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ሊያደርግ እንደሚችል እረዳለሁ።

የምግብ አያያዝ ባለሙያ ስም፦________________________________________

የምግብ አያያዝ ባለሙያ ፊርማ፦______________________________ቀን፦__________

የPIC ፊርማ፦____________________________________ቀን፦__________



Southern Nevada Health District
280 S. DECATUR BLVD. · LAS VEGAS, NV 89107 · (702) 759-1110 · WWW.SNHD.INFO